# በዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ የተመራው የኢጋድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ልዑክ ከፕሬዝዳንት ሳልቫ ኪር ማያርዲት ጋር ተወያየ

ፕሬዝዳንት ሳልቫኪር በቤተመንግስታቸው ነው ልዑኩን የተቀበሉት፡፡ ዶክተር ወርቅነህ በኢጋድ ከፍተኛ ልዑክ በኩል ለደቡብ ሱዳን ሰላም ስምምነት ትግበራ እየተደረጉ ስላሉ ጥረቶች ለፕሬዝዳንት ሳልቫ ኪር ገለጻ አድርገውላቸዋል፡፡



የኢጋድ አባል አገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በደቡብ ሱዳንን "አገር አቀፍ የምክክር መድረክ" (National Dialogue) እንደሚደግፉም ገልጸዋል፡፡

ፕሬዝዳንት ሳልቫ ኪር ማያርዲት በበኩላቸው በቅርቡ በካምፓላ (SPLM) የተደረገውን የሱዳን ህዝቦች ነጻነት ንቅናቄ የውህደት ሂደትን ለሚኒስትሮቹ ገለጻ አድርገውላቸዋል፡፡ ይህም የሰላም ስምምነቱን ለመተግበር የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት ታምኖበታል፡፡

ለሰላም ስምምነቱ ትግበራ ድጋፍ እንደሚያደርጉም ፕሬዝዳንት ኪር ለሚኒስትሮቹ ገልጸውላቸዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ 58ኛው የኢጋድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች መደበኛ ስብሰባ በደቡብ ሱዳን ጁባ ተካሂዷል፡፡ የደቡብ ሱዳን የሰላም ስምምነት በአዲስ መልክ በተጠናከረ መልኩ እንዲተገበር ተቀናጅቶ ለመስራት ሚኒስትሮቹ ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡

*የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር*

*ቃልአቀባይ ጽ/ቤት*

*ሃምሌ 17 ቀን 2009 ዓ.ም*